*AMHARIC*

SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

ኖቨምበር(ህዳር) 11, 2008

የተከበራችሁ ወላጆችና የቤተሰብ አባሎች፤

በቅርቡ ተማሪዎቻችንና ሌሎች ወጣቶችን በሚመለከት በኮሚኒቲያችን ስለተከሰተው ጉዳይ እንዳሳሰባችሁ አውቃለሁ። በሲያትል ህዝባዊ አብያተ ትምህርት የሚገኙ እያንዳንዱ ሰው እንደዚሁ አሳስቦታል። በተማሪዎቻችን ላይ የተፈጸመ ወይም ተማሪዎቻችን የፈጸሙትን ማንኛውም ሁከት በሚመለከት ያለን የትእግስት ፖሊሲ ዜሮ መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ይህንን ደብዳቤ የጻፍኩበት ምክንያት በትምህርት ቤት የልጅዎ ደህንነት የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዱን እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆናችንን እንድታውቁት ለማድረግ ነው።

ተማሪዎቻችን ደህንነት የተሞላበት ኮሚኒቲን ለማስፈን ሁላችንም በጋራ እንደምንሰራ እንዲተማመኑብን ያስፈልጋል። ተማሪዎች ገና ሊከሰቱ የታሰቡ ወይም የተከሰቱ አጋጣሚዎችን በሚመለከት ማስታወቅ እንደሚኖርባቸው ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑ እንዲያውቁት ለማድረግ የርስዎን ድጋፍ እንሻለን። ተማሪዎች ሊከሰቱ የታሰቡ ወይም የተከሰቱ ሁኔታዎችን ላለመናገር ይመርጡ ይሆናል። ምክንያቱም አጸፋዊ ጥቃት ይወሰድብናል ወይም "አቃጣሪ" " ስኒች" ተብለው እንዳይጠሩ በመፍራት ነው። ልጆቻችንን ደህንነት ለመጠበቅ እብረን እንድንሰራ ሊፈጸሙ የታሰቡና ፡ የተፈጸሙ ነገሮች ሁሉ እንዲገልጹልን ወጣቶቻችንን በሃይል ማስታጠቅ ይገባናል።

ተማሪዎች፣ ቤተሰቦችና የኮሚኒቲ አባላት ሁኔታዎችን የሚያሳውቁበት ብዙ መንገዶች አሏቸው። እነዚህ ጥቆማዎች በአፋጣኝ መልስ እንድንሰጥና የመከላከያ እርምጃዎችን እንድንወስድ ያስችሉናል። ለደህንነት አስጊ የሆነውን ዛቻ እንድንመረምርና እንደአስፈላጊነቱ ደግሞ ሌሎች ባለስልጣኖችን በጉዳዩ እንዲሳተፉ ለማድረግም ይጠቅመናል።

ጉዳዮችን ለማሳወቅ ከሚቻልባቸው አማራጮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፤

- ለድንገተኛ ሁኔታ ወይም ለአፋጣኝ እርዳታ 911 መደወል። እንዲሁ ለሜትሮ ትራንዚትም ጭምር።
- ወደ ሲያትል ኣብያተ ትምህርት የደህንነትና የጥበቃ ዲፓርትመንት በቴሌፎን ቁጥር (206) 252-0707 መደወል።
- ድንገተኛ ላልሆኑ ጉዳዮች ወደ ሜትሮ ትራንዚት ፖሊስ በቴሌፎን ቁጥር (206) 296-3311 መደወል።

እባክዎን ተማሪዎ አስጊ የሆኑ ሁከቶችን ሁሉ ወይም ወደ 'አስጊ ደረጃ ሊደርሱ የሚችሉ ወሬዎችን በሚሰሙበት ወቅት ማሳወቅ እንደሚኖርባቸው ያነጋግሯቸው። ከዚህ በታች በተገለጹት መንገዶች ማንነታቸው ሳይታወቅ ማሳወቅ ይችላሉ፤

- **በሚስጢራዊነት የደህንነት የትምህርት ቤቶች ቀጥታ መስመር** (206) 252-0510
- **በሚስጢራዊነት ወንጀል ማስቆሚያ መረጃ መስጫ መስመር** : 1-800-222-TIPS (8477) **ወይም** (206) 343-2020
- **ሚስጢራዊ ወንጀል ማስቆሚያ የጽሁፍ መልእክት(ቴክስት ሜሰጅ) ለሲያትል ፖሊስ ዲፓርትመንት** 1) **ለ** "TIP486" **ብለው ይጻፉ**; 2) **መልእክትን ጻፍ**; 3)**ለ** "CRIMES" **ወይም** "274637." **መልእክትን ላክ። የጽሁፍ መልእክቱ እንደደረሰ ላኪው የማረጋገጫ ቁጥር በ** 10 **ውስጥ ወይም ባነስ ሰከንድ ጊዜ መድረሱን በመግለጽ ይላክላቸዋል።**

ወላጆች፣ ቤተሰብ አባላትና ሌሎች በኮሚኒቲ የሚገኙ ይህንን ሪፖርት የማድረግ አማራጮች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

ተማሪዎቻችን በትምህርት ቤት ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለማረጋገጥ እየሰራን ቢሆንም ጉዳዩ ከትምህርት ቤት ክልል ውጭ ያልፋል። በርግጥ ተማሪዎቻችን በትምህርት ቤት ክልል እያሉ ደህንነት እንደሚሰማቸውና ነገር ግን ትምህርት ቤትን ለቀው በሚወጡበት ጊዜ ይህ ደህንነት እንደማይሰማቸው ገልጸውልናል። በቅርቡ የተፈጸሙት በርካታ ፍጻሜዎች ከትምህርት ክልል ውጭ የተፈጸሙ ናቸው። አንዳንድ ጊዜም በትምህርት ቤቶቻችን የማይማሩ ወጣቶችም ይገኙበታል። አንድ አጋጣሚ መከሰቱን በምናውቅበት ወቅት ከሲያትል ፖሊስ ዲፓርትመንት፣ ፓርክስ ዲፓርትመንት፣ ሜትሮ፣ የወላጆች ድርጅቶችና በኮሚኒቲ ከሚገኙ የስራ ባልደረቦቻችን ጋር በቅርብ አብረን እንሰራለን። በጋራ በመስራት ወጣት ተማሪዎቻችን ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ የመከላከያ እርምጃዎችን እንድንወስድ ያስችለናል።

በዚህ አመት የደህንነትና የጸጥታ ዲፓርትመንቻችን ለተማሪዎቻችን ተጨማሪ እርዳታዎችን ለመስጠት በአዲስ መልኩ ተጠናክሯል። በተጨማሪ ከትምህርት ሚኒስቴር "ለትምህርት ቤት ደህንነት ዝግጁነትና አስቸኳይ ግብረ መልስ"( "Readiness and Emergency Response for School Safety") በሚል የ $500,000. ዶላር እርዳታ አግኝተናል። ይህ ገንዘብ ለትምህርት ቢቶች ተጨማሪ ስልጠናዎችን ለመስጠት፣ እቃዎችን ለመግዛትትና ድጋፍን ለመስጠት ያስችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ የተለያየ አማራጭ የትምህርት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን የትምህርት ፕሮግራምና የተቀናጀ የጣልቃ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችል የድጋፍ ሰጪና ጣልቃ ገቢ ኣገልግሎት ሰጪ ዲፓርትመንታችንን በአዲስ መልኩ እንዲጠናከር አድርገናል። እንዲሁም ወጣቶችን ከሁከት ለመከላከል በሚያስችል ፕላን ላይ ከሲያትል ከተማ ጋር በትጋት አብረን እየሰራን ነው።

(Over)

ዋናው ቁም ነገሩ፡ ሁሉም ልጆቻችን የተጠበቁ እንዲሆኑ ይገባቸዋል። አስተዳዳሪ እንደመሆኔ የተማሪዎቻችንን ደህንነት ለማስጠበቅ በመውሰድ ላይ ያለነውን እርምጃ እንድታውቁት እተጋለሁ። የሚያሳስባችሁና ነገር ካለና ጥያቄ ካላችሁ ተማሪዎ በሚማርበት ት/ቤት የሚገኙትን የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ተገናኙ። ወቅታዊና ተጨማሪ መረጃዎች በየወቅቱ በዌብሳይታችን እንዲወጣ እናደርጋለን። http://www.seattleschools.org/area/m_news/index.dxml.

Sincerely,



Maria L. Goodloe-Johnson, Ph.D.
Superintendent


ATTN: 32-150
Seattle School District #1
P. O. Box 34165
Seattle, WA 98124-1165


**Non Profit Organization**
**U.S. POSTAGE**
**P A I D**
**Seattle, WA**
**Permit No. 3904**